07

5ኛ ዓመት ቁጥር 49
5th Year N° 49

ባህር ዳር ሐምሌ 29 ቀን 1992
Bahir Dar 5th August 2000

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 3.30	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.BOX

አዋጅ ቁጥር 49/1992 ዓ ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገፅ 7	Proclamation N°49 /2000 A Proclamation To Provide For The Establishment Of Lake Tana Transport Enterprise Page 7

አዋጅ ቁጥር 49/1992 ዓ ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅትን
ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ጽ/ቤት አሁን ያለበትን አስተዳደራዊ ችግሮች በመፍታት የበለጠ አቅም ፈጥሮ ቀጣይነት ያለው ተግባር እንዲያከናውን የነበረው ጽ/ቤት የጠራ ዓላማ፣ ተግባርና ድርጅታዊ አቋም ያለው አካል አድርጎ በአዲስ መልክ ማደራጀት በማስፈለጉ፣

የገቢያ ህጎችን ተከትሎ በጣና ኃይቅ ላይ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ብቃት ያለውና ከአካባቢ ብክለት የጸዳ የውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት የማደራጀትና የማሰፋፋት፣ በዘርፉም የሚኖረውን የአገልግሎት ዋጋ የማረጋጋት ሚና ያለውና ራሱን የቻለ ሕጋዊ አካል ማቋቋም በማስፈልጉ፣

ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር የሚያከናውናቸውን ተግባራት በግልፅ ለይቶ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 49 ንውስ አንቀጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል::

PROCLAMATION N° 49 /2000
A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF LAKE TANA TRANSPORT ENTERPRISE

WHERE AS, it has become necessary, solving the existing administrative problems, to re establish the previous Lake Tana transport office by making more capable to perform continuing activity having definite objective, duity and organizational structure;

WHERE AS, believing that it is necessary to establish legal body that could organize and promote water transport services in lake tana which is safe, adequate and free from environmental pollution, and playing the role of stabilizing service fee in the sector following the market law;

WHERE AS, it has become necessary to clearly stipulate the activities of the enterprise based on the objective of its establishment;

NOW, THERE FORE, council of the Amhara National Regional State pursuant to sub article 3/1 of article 49 of the constitution is here by

379 ~~297~~

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልል የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 49/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ፣

1. "ድርጅት" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመው የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት ነው።
2. "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የተቋቋመ የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ነው።
3. "ወደብ " ማለት በጣና ኃይቅ ዙሪያና መሐል ደሴቶቹ ላይ የተገነባ ወይም ለወደፊት የሚገነባ፤ ለጀልባዎች መጠጊያ ፣ ለተሣፋሪዎች መሣፈሪያና መውረጃ፣ ለዕቃዎች መጫኛና ማራገፊያ አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ ነው።
4. " ኃይቅ " ማለት የጣና ኃይቅ ማለት ነው።
5. "ጀልባ" ማለት በውሃ ላይ በሞተር ወይም ያለሞተር በውሃ መቅዘፊያ መሣሪያዎችና በንፋስ የሚንቀሳቅስ ሆኖ ተሣፋሪዎችንና ዕቃዎችን በውሃ ላይ ለማጓጓዝ፣ እንዲሁም በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትን ለማጥመድና ሌሎች ተግባራትንም ለማከናወን የሚያገለግል ነው።

ክፍል ሁለት
ስለድርጅቱ መቋቋም ፣ ተጠሪነት ፣አደረጃጀትና ዓላማ

3. ስለድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት

1. የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ድርጅት እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግስታዊ የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ድርጅቱ ከዚህ በፊት በሥሩ ያስተዳድራቸው የነበሩ ተንቀሣቃሽና የማይንቀሣቀሱ ሀብቶችን መነሻ ካፒታሉ አድርጎ ተቋቁሟል።
3. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የክልሉ መንግስት ለሚሰይመው የሥራ አመራር ቦርድ ይሆናል።

4. የድርጅቱ አደረጃጀት

1. የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት በባሕርዳር ከተማ ይሆናል።
2. ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎች የማቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

proclaimed as follows.

PART ONE
General

1. Short Title

This Proclamation may be cited as" The Amhara National Region Lake Tana Transport Enterprise Establishment Proclamation N° 49/ 2000"

2. Definitions

Unless the context requires other wise in this proclamation:

1. "Enterprise" means Lake Tana transport enterprise established pursuant to this proclamation.
2. "Board" means the managing board of lake tana transport enterprise established pursuant to article 8 of this proclamation.
3. "Port" means an area build or to be build around or in Lake Tana to give services like boats stop, embarkation and disembarkation of passengers, load and unload goods.
4. "Lake" means Lake Tana
5. "Boat" means small hollow structure moved by oars, sails or a motor use for transporting passengers and goods, as well as fishing and other activities.

Part Two
Establishment, Accountability, Organization and Objectives of the Enterprise

3. Establishment and Accountability of the Enterprise

1. Lake Tana Transport office here in after refered to as "The Lake Tana Transport Enterprise" is here by established as an autonomous development enterprise having legal personality under this proclamation.
2. The enterprise is established, by making the movable and immovable assets administered under the previous office as its initial capital.
3. The enterprise, being established for a specified period of time, shall be accountable to the executive committee of the Amhara National Regional State and the managing board assigned by the same.

4. Organization of the enterprise

1. The head office of the enterprise shall be in Bahir Dar.
2. The enterprise may have branch offices to be

5. የድርጅቱ ዓላማ

የድርጅቱ ዓላማ ጥራትና ብቃት ያለው፣ የተሣፋሪዎቹን እና የዕቃዎችን ደህንነት የጠበቀ የውሃ ላይ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠትና ማስፋፋት ነው።

ክፍል ሦስት

የድርጅቱ ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር እና ድርጅታዊ አቋም

6. ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር

ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ከአካባቢ ብክለት በፀዳ ሁኔታ በኃይቁ ላይ ሰውንና ዕቃን በጀልባ በማጓጓዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል ፣
2. ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ጎብኝዎች በጀልባ የማስጎብኘት አገልግሎት ይሰጣል ፣
3. ለመንገደኞችና ለአገር ጎብኝዎች በወደቦቹ ላይ የመዝናኛ ቦታዎችን በመሥራት የመስተንግዶ አገልግሎት ይሰጣል፣
4. አሸዋ አምርቶ በጀልባ በማጓጓዝ ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ ለሽያጭ ያቀርባል ፣
5. ወደቦችን፣ መጋዝኖችን፣ ለውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚረዱ የሬዲዮና ምልክት መስጫ ማማዎችን፣ የትራፊክ ምልክቶችን፣ እንዲሁም የተንሣፋፊ በርሜሎችን ይሰራል፣
6. የአነስተኛና የትላልቅ ጀልባዎችን አካል ይሠራል፣ ይጠግናል፣ እንዲሁም የጀልባ ሞተሮችን ጥገናና ተመሣሣይ ሥራዎችን ያካሂዳል፣
7. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ያስተዳድራል፣ በስሙ ይከሣል ይከሠሣል፣
8. በስሙ ገንዘብ ይበደራል፣ ከሚሠጣቸው አገልግሎቶችም ገቢዎችን ይሰበስባል ፣
9. የዕቃና የመንገደኞችን ደህንነት ይጠብቃል ፣
10. የውሃ ላይ ትራንስፖርትን በሚመለከት አመቺ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችንና ማቴሪያሎችን በሥራ ላይ ለማዋል ሥልቶችን ይቀይሳል
11. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያግዙትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል ፣

7. ድርጅታዊ አቋም

ድርጅቱ፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. አንድ ሥራ አስኪያጅ እና
3. ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈልጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል።

ክፍል አራት

የድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ አወቃቀር፣ ተጠሪነት፣ ሥልጣንና ተግባር

established in other places as may be necessary.

5.Objective of the enterprise

The objective of the enterprise is to promote and provide adequate and efficient safe water transport service for passengers and goods.

Part Three

General Duties Powers and Organizational Structure of the Enterprise

6.General duties and powers of the enterprise

The enterprise shall have the following powers and Duties to:

1. render transport service under the condition free from environmental pollution, for passengers and goods on lake by boat;
2. provide tour services for foreign and indigenous tourists;
3. render different services for passenger and tourists by constructing recreational places along the ports;
4. produce sand and transport by boat to provide for the beneficiaries for sale;
5. construct ports, stores, radio and water towers that help for marine transport service as well as traffic symbols and floater barrels;
6. construct and maintain the bodies of small and big boats, as well as perform the maintenance of the motors of boats and similar works;
7. owned and administer property; sue and be sued in its own name;
8. loan money in its own name; collect revenue from the service it renders;
9. maintain the safety of passengers and goods;
10. design strategies for the implementation of appropriate technologies and materials concerning marine transport;
11. perform such other related activities that may help to execute its objectives;

7. Organizational structure

The enterprise shall have:

1. a managing board
2. a manager and
3. other responsible persons and markers necessary on each level of the structure.

Part Four

Organization, Accountability, Powers and Duties of the Managing Board of the Enterprise

381

381 ~~293~~

8. የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አወቃቀርና የሥራ ዘመን

1. የሚዋቀረው የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል፣
2. የቦርዱ አባላት እና ሰብሳቢዉ በክልሉ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሰየማሉ፣
3. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን እና አበል በክልሉ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወሰናል፣

9. የቦርዱ የስብሰባ ሥርዓት

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምጹ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣን ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

10. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ በመምረጥ ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያሾማል።
2. ለሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑትን የሥራ ኃላፊዎች ምደባ፣ ቅጥር፣ የደረጃ እድገት፣ ዝውውርና ስንብት ያፀድቃል።
3. ድርጅቱ የሚሠራበትን አጠቃላይ ፖሊሲ አመንጭቶ በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለማፀደቅ ያቀርባል፣ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል።
4. የድርጅቱን ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል።
5. ድርጅቱ በመዋቅር፣ በሰው ኃይል፣ በመሣሪያና በሥራ አመራር የሚጠናከርበትን መንገድ ያስጠናል፣ ጥናቱንም ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።
6. የድርጅቱን ንብረት በአግባቡ መያዙን፣ የገንዘብና የሰው ኃይል አጠቃቀሙም የክልሉን የኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ዓላማዎች እንዲሁም የድርጅቱን ዓላማ ለማስፈፀም ብቁ መሆኑን ያረጋግጣል።
7. በድርጅቱ የሚቀርብለትን የትራንስፖርት ታሪፍ፣

8. Members organization and term of services of the managing board

1. The managing board to be established shall be accountable to the executive committee of the Amhara Nationa Regional State and shall consist 5-7 members;
2. The members and chair man of the board shall be appointed by the executive committee of the regional state;
3. The term of service and allowance of the members of the board shall be determined by the executive committee of the Regional State;

9. Meeting procedures of the board

1. The regular meeting of the board shall convene once in every three months. However, extraordinary meeting shall be held at any time as may be necessary.
2. The presence of above half of the members shall constitute a quorum.
3. Decision of the board shall be passed by a majority vote. However, in case of a tie, the chairperson shall have a costing vote.
4. With out prejudice to the provision of this article, the board may adapt its own rules and meeting procedures.

10. Powers and duties of the board

The board shall have the following powers and duties to

1. select and present the manager of the agency for appointment to the executive committee of the region;
2. approve the employment, assignment, transfer and dismissal of heads accountable to the manager;
3. initiate and present for approval, the general guiding policy of the enterprise to the executive committee of the region; and follow up its implementation;
4. approve the budget and action plan of the enterprise and follow up its implementation;
5. cause the study of the mechanisms by which the enterprise is going to be strengthen in man power, equipment and management and implement the same when it found vital;
6. insure the proper handling of the property of the enterprise and its utilization of finance and manpower for efficient execution of the economic and social objective of the region as well as the objective of the enterprise;
7. approve transport tariff, stores and ports service

382

382 ~~387~~ ~~406~~

የመጋዝኖች ኪራይ፣ የወደቦች አገልግሎት ኪራይ፣ ሌሎችን የድርጅቱን አገልግሎቶችና ምርቶች ዋጋ እየገመገመ ያፀድቃል።

8. በድርጅቱ የሚቀርቡትን ጉዳዮች እየመረመረ ውሳኔዎችን ያፀድቃል፣

9. እንደአስፈላጊነቱ የየወቅቱን የገቢያ ዋጋ እና የድርጅቱን አቅም እየገመገመ የንብረቶቹን ሽያጭ ፣ ግዢ ፣ ጥገና እና ግንባታ በተመለከተ የሥራ አስኪያጁ የሥልጣን ገደብ ይወስናል።

10. የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ብድሮችን ያፀድቃል፣ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ብድሮችን እያስጠና ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስወስናል።

11. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያወጣል ፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል።

12. ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል።

ክፍል አምስት
ስለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ

11. የሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያ ከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የሥራ አመራር ቦርዱ አባልና ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል።

2. የድርጅቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል።

3. የድርጅቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ የድርጅቱን የሥራ መዋቅር ደመወዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርዱ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።

4. የድርጅቱን ገንዘብ ለማንቀሳቀስ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል።

5. የፖሊሲ ሃሣቦችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

6. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

7. የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣ በጀት እና የሥራ ፕሮግራም እያዘጋጀ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ ያውላል።

8. ለሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባ፣ የደረጃ ዕድገት፣ ዝውውር፣ የዲስፕሊን ጉዳዮችንና ስንብትን በሚመለከት ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል።

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው ሕግና በድርጅቱ

rent, other services and productions prices of the enterprise presented to it by the same;

8. examine and pass decisions up on cases presented to it by the enterprise;

9. decide the limit of the power of the manager concerning the sales, purchase, maintenance & building activity, when find necessary upon the evaluation of the timely market price and the potential of the enterprise;

10. approve medium term loans and also cause studies on long term loans and present the same for approval;

11. issue different directives which help for the implementation of this proclamation and follow up the implementation;

12. submit periodic reports to the executive commiitee of the region;

Part Five
The Manager of the Enterprise

11. Powers and duties of the manager

The manager of the enterprise shall in addition to the powers and duties vested in the enterprise as enumerated under article 6 of this proclamation have the power and duties to:

1. serve as a member and secretary of the managing board;

2. direct, administer and supervise the activities of the enterprise;

3. organize the office, prepare and submit to the board for approval the organizational structure, salary and allowances of the enterprise; and follow up its implementation;

4. open bank account to run the finance of the enterprise;

5. initiate policy issues and upon approval implement the same;

6. prepare directives that help for the execution of this regulation and upon approval implement the same;

7. prepare and Submit to the board, short, medium and long term plan, budget and action plan of the enterprise; and implement the same up on approval;

8. submit to the board for approval, concerning the employment, assignment and dismissal of heads of the enterprise accountable to the general manager;

9. with out prejudices to the provision of sub article 8 of this article, employee, administer, promote

የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል።

10.የዕቃና የመንገደኞች ትራንስፖርት፣ የቱሪስት ማስጎብኘት፣ የመጋዝኖች ኪራይ፣ የወደቦች ኪራይና ለሚሠጣቸው ሌሎች አገልግሎቶች የታሪፍ መጠን እያጠና በቦርዱ ያስወስናል።

11.ለድርጅቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ እንዲሆን ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል።

12.ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገዉ ግንኙነትና ዉሴታ ሁሉ መ/ቤቱን ይወክላል።

13.የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

14.የየሩብ ዓመቱንና ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል።

15.በቦርዱ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የድርጅቱ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር

1. የድርጅቱ ሠራተኞች ቅጥር እና አስተዳደር በአሰሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ የሠራተኛ ማስተዳደሪያ የውስጥ ደንብ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል።

13. የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ

የድርጅቱ በጀት የሚገኘው ከሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች ይሆናል፦

1. ከውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት ፣ ከመዝናኛ አገልግሎት ፣ ከአሸዋ ምርትና በተጓዳኝ ከሚሠሩት ተግባራት ከሚገኙ ገቢዎች ፣

2. ከባንክና ከሌሎች ድርጅቶች ከሚገኝ ብድር እና

3. ከሌሎች::

14. የድርጅቱ የበጀት ዓመት

የድርጅቱ የበጀት ዓመት ከመንግስት የበጀት ዓመት ጋር አንድ ነው::

15. የሂሣብ መዛግብትና ምርመራ

1.ድርጅቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፣

2.አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የድርጅቱን የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች አያያዝን

and dismiss its employees in accordance with the appropriate law and administrative regulation of the enterprise;

10.study and Submit for approval tariff for passengers and goods transport and tourists tour, stores and ports rent, and tariff for other services it renders;

11.cause expenditure in accordance with the approved budget and plan of action of the enterprise; and supervise the implementation of the same;

12.represent the enterprise in its dealings with other third parties;

13.execute, and cause the execution of the decision of the board;

14.prepare and submit, quarterly and annual activity performance and financial reports, to the executive committee and the managing board of the region;

15.perform such other duities assigned by the board;

Part Six
Miscellaneous Provisions

12. Employment and administration of the staffs of the enterprise

1.Employment and administration of the staff of the enterprise shall be effected in accordance with labor proclamation.

2.With out prejudices to the provision of sub article 1 of this article, the enterprise shall prepare its employment administrative regulation as may be necessary; and up on approval implement the same.

13. Budget source of the enterprise

The budget of the enterprise shall be drawn from the following financial sources:

1.Revenues obtained from water transport services, recreational services, and productions and other activities,

2.Loans obtained from banks and other organizations and

3. from others.

14. The budget year of the enterprise

The budget year of the enterprise shall be the same with the budget year of the government.

15. Books of accounts and auditing

1.The enterprise shall keep appropriate & complete books of accounts

2.The board shall utilize accepted accounting procedures. concerning the handling of the books

384

~~408~~ 384

በተመለከተ ቦርዱ ተቀባይነት ያላቸው የሂሣብ አሠራሮችን ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይችላል፣

3. የድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በክልሉ ዋና አዲተር ወይም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ::

16. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

የጣና ኃይቅ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለድርጅቱ ተላልፈዋል::

17. ስለ ትርፍ አደላደል

የድርጅቱን የተመረመረና የተጣራ ትርፍ አደላደል በሚመለከት ቦርዱ ለክልሉ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስወስናል::

18. የኃላፊነት ወሰን

ድርጅቱ በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጠቅላላ ያለውን ንብረት እስከሚሸፍነው ድረስ ብቻ ነው::

19. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ድርጅቱ ያስተዳድራቸው የነበሩትን የአትክልት ቦታዎች በተመለከተ የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወሰነው መሠረት ይፈፀማል፣

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአትክልት ቦታዎቹ ላይ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ድርጅቱ ባለበት ሁኔታ ሊያስተዳድራቸው ይቆያል::

20. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባሕርዳር
ሐምሌ 29 ቀን 1992
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

of accounts and financial documents of the enterprise, as may be necessary.

3. The Enterprise's books of accounts shall be audited once in every year by the Regional Auditor General or by another auditor assigned by the board.

16. Transfer of right and obligation

The rights and obligation of Lake Tana transport office is here by transferred to the enterprise pursuant to this proclamation

17. Profit allocation

The board shall present to the executive committee of the regional state for decision concerning the payment of the audited net profit of the enterprise.

18. Scope of liability

The enterprise shall be held liable only to the extent of its total assets.

19. Transitional provisions

1. The issues concerning the garden areas administered by the enterprise prior to the coming in to forth of this proclamation, shall be executed up on the decision of the regional executive committee.

2. With out prejudice to the provisions of sub article 1 of this article until the decision is passed the enterprise will administer the garden areas in the condition they are.

20. Effective date

This proclamation shall enter in to force on the date of its publication in the Zikre Hig Gazette.

Done at Bahir Dar
This 5th day of August 2000
Council of the Amhara National Regional State

385

385

297